

# የትንቢት ቃል

አምስተኛ ዓመት,ቁጥር 1

መጋቢት 2003

## «የሰንበትን ቀን አስብ...» በኢትዮጵያ ታሪክ

የክርስትና ሃይማኖት አመጣጥ በኢትዮጵያ ውስጥ የረጅም ጊዜ ታሪክ አለው። ይህም ታሪክ ከብሉይ ኪዳን ጊዜ ነው የጀመረው።

በአባቶቻችን አማካኝነት የደረሰንን የመጽሐፍ ቅዱስ ውርስ ማስታወስና መጠበቅ የኛ ኃላፊነት ነው። ከዚህም ታሪካችን ዛሬ መማር እንችላለን። ነብዩ ኤርምያስ ሕዝቡን የጥንቱን ጊዜ እንዲጠይቁ ሲያስታውሳቸው፤ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን መልእክት (ቃል) ሲከተል (ሲታዘዝ) የነበረበትን ጊዜ በማሰብ ነው (ኤር 6፥16)። ስለዚህ የክርስትናን ታሪክ በኢትዮጵያ መለስ ብለን ስንመለከት ልንጠብቀው የሚገባን የመጽሐፍ ቅዱስ ውርስ እንዳለን እንመለከታለን። ከነዚህ ውርሶች መካከል አንዱ ልንረሳው የማይገባን «ሰንበት» ነው።

ኢትዮጵያ የክርስትናን ሃይማኖት ከመቀበልዋ በፊት ከአይሁዶች እምነት ጋር መተዋወቋን የሚያሳዩ ብዙ ፍንጮች አሉ። አንዳንድ በሙሴ መጻሕፍት የምናገኛቸው ትእዛዛት እስከዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክ ይጠበቃሉ። ለምሳሌ ያህል፥- የወንዶች በስምንተኛ ቀን መገረዝ፣የተፈቀደና ያልተፈቀደ መብል (በተለይ የአሳማ ሥጋ አለመበላት)፣ ከዚያም ባሻገር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሲጠቀስ የምናገኘው የሳምንት 2 ጊዜ የመጾም ልምድ እስከዛሬ የብዙ የአገራችን ክርስቲያኖች ልምድ ነው (ሉቃ 18፥12)።

<u>የሰንበት ታሪክ በኢትዮጵያ</u>

እስከዛሬ የክርስትናን ሃይማኖት በኢትዮጵያ ከቀረጹት ከላይ ከተጠቀሱት የአይሁድ እምነት ልምዶች ሌላ ሰንበትም (ቅዳሜ) ከአይሁዶች ወደአገራችን የመጣ ውርስ ነው። ሰንበት ከክርስቶስ ልደት በፊት ለመጠበቁ ማስረጃ የሚሆኑ ግልጽ ጽሑፎች ባይኖሩም የተለያዩ ምክንያቶች ሰንበት በኢትዮጵያ ይጠበቅ እንደነበር (መከበሩን) ያመለክቱናል። ለምሳሌ ወደ ኢየሩሳሌም ለአምልኮ ተጉዞ የነበረውና ወደ አገሩ ሲመለስ የኢሳያስን መጽሐፍ ሲያነብ የነበረው ጃንደረባ ታሪክ ኢትዮጵያ ከክርስቶስ በፊት ከዕብራዊያን እምነት ጋር መተዋወቋን ይጠቁመናል። ይህ የንግስት ህንደቄ አዛዥ እና የገንዘብ ያዥ ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር (ሐዋ ሥራ 8፥27-28)።

<u>የሰንበት ጥያቄ በኢትዮጵያ በ13ኛው ክ/ዘ</u>

የአሌክሳንድሪያ (ግብጽ) ተዋህዶ ቤ/ክ በ 5ኛው ክፍለ ዘመን የሰንበትን ማክበር ቀስ በቀስ በመተው እሁድን እንደ ጌታ ቀን ማስፋፋት ጀመረ። በዚያን ጊዜ የአሌክሳንድሪያ ቤ/ክ በኢትዮጵያ ቤ/ክ ሕልውና ላይ ታላቅ ተፅዕኖ ነበረው። አንድ ምሳሌ ለመጥቀስ በዚያን ዘመን የኢትዮጵያ ቤ/ክ መሪዎች (አቡነ) ከአሌክሳንድሪያ ቤ/ክ መሾማቸው ነው። በ 4ኛው ክ/ዘ ልክ በግብጽ ይደረግ እንደነበረው እስከዛ ጊዜ ድረስ በኢትዮጵያም «ሰንበትና እሁድ ሁለቱም ቀኖች ይከበሩ (ይጠበቁ) ነበር» የሚል ግምት አለ። ይህም ሊሆን የቻለው ኢትዮጵያ በ340 ዓ.ም. በይፋ የክርስትና ሃይማኖትን በንጉስ እዛና አማካኝነት ከተቀበለች ጊዜ ጀምሮ ነው (ዋቢ፥- Werner Vyhmeister, „The Sabbath in Egypt and Ethiopia“, pg.174)።



በመጀመሪያ የአሌክሳንድሪያ ቤ/ክ «ሰንበትን አትጠብቁ!» ብላ ኢትዮጵያን አላስገደደችም። ቢሆንም ከግብጽ ይላኩ በነበሩት አቡነዎች አማካኝነት ይህ ተፅዕኖ በበለጠ ይታይ ነበር። በ13ኛው ክ/ዘ ግልጽ በሆነ መንገድ ሰንበትን ለማስተው (ለማስቀረት) ተሞከረ (ዋቢ፥- Vyhmeister, pg. 175)። ይህ ሙከራ በኢትዮጵያ ታላቅ ተቃውሞን አስከተለ። በዚህም ምክንያት በወቅቱ የኢትዮጵያ ንጉሥ የነበረው ዘረ ያዕቆብ ኢትዮጵያ ስለ ሰንበት ያላትን አቋም በዝርዝሩ የገለጸበትን የቤ/ክ መመሪያ አወጣ። በዚህ መመሪያ ውስጥ ሰንበትና እሁድ ሁለቱም እንዲጠበቁ አዘዘ። ይሄም «የሐዋሪያት ልምድና ትእዛዝ ነበር» ብሎ ተናገረ። ይህ የቤ/ክ መመሪያ በሰንበት ቀን መደረግ የሚፈቀዱትን ሥራዎች ሁሉ ሳይቀር ይተነትናል። ለምሳሌ፥- እርሻ ማረስ፣እንጨት መፍለጥ፣እህል መፍጨት፣... (ዋቢ፥- Hammerschmidt Ernst, Münster 1963, pp. 25,26)። የሰንበትን ቀን ማክበር አስፈላጊ እንደሆነ ምክንያት ለመስጠት መጽሐፍ ቅዱስን በመጥቀስ የሰጠው አገላለፅ የሚያስገርም ነው፥-

«የክርስቶስ ቤ/ክ የተመሠረተችው በሕግና በነቢያት፣በወንጌልና በሐዋሪያት ነው። ማቴዎስ ምእራፍ 5፥18 እና ሉቃስ ምእራፍ 16፥17 ላይ እንዳለው ሕግ፤በተለይ 10ቱ ትእዛዛት በአዲሱ ኪዳን ዘመንም መጽናታቸው ተገልጾአል። ይህንን ሃሳብ ያዕቆብ 2፥10 ይደግፋል። በዚያ መሠረት ከ10ቱ አንዱን የሚደመስስ የቤ/ክንን መሠረት ያፈርሳል» (ዋቢ፥- Hammerschmidt, pg. 23)

«ሰንበትን የሚያስወግደውን ሰው በተመለከተ እርሱ የቤ/ክ መሠረት አፍርሶአል። ምክንያቱም ከተመሰረተችበት ሕግ አንዱን አስፈላጊ ቃል አውጥቶአልና። ከ10ቱ ትእዛዛት አንዱን ቃል የሚሰርዝ የየሱስን ስም እንደሰረዘ ይቆጠራል፣የየሱስን ስም የሰረዘ ደግሞ የሥላሴን ስም ሰረዘ ማለት ነው፣ከሥላሴ አንዱን ሰረዘ ማለት ደግሞ ራሱን ከክርስትና ሃይማኖት ሰረዘ ማለት ነው» (ዋቢ፥- Vyhmeister, pg. 178)

<u>የሰንበት ጥያቄ በኢትዮጵያ በ16ኛው ክ/ዘ</u>

እ.ኤ.አ. በ1507 ዓ.ም. ኢትዮጵያ በእስላም ልትጠቃ ስለነበር የኢትዮጵያ ንግሥት ሄሌና የፖርቱጋልን እርዳታ ጠየቀች። የርሷን ጥያቄ በመስማት ፖርቱጋል በ1520 ዓ.ም. መልእክተኞችን ወደ

***<u>በገጽ 3 ይቀጥላል</u>***

### በዚህ እትም ውስጥ

| | |
|---|---|
| *«የሰንበትን ቀን አስብ...» በኢትዮጵያ ታሪክ* | 1 |
| *ከአዘጋጆች* | 2 |
| *ምትን ልሞክረው* | 2 |
| *ከአንባቢዎች* | 2 |
| *መሰብሰባችንን አንተው* | 3 |
| *የአካል እንቅስቃሴ ጥቅም* | 4 |
| *ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት - ክፍል 5* | 5 |
| *መጠበቂያው የእግዚአብሔር ቃል* | 6 |
| *የየሱስ አሻራ ያለበት ለዘላለም አይጠፋም* | 7 |
| *ወቅታዊ ዜናዎች በአጭሩ* | 7 |
| *የጥያቄዎ መልስ* | 8 |

# ከአዘጋጆች



***የተወደዱ አንባቢ ሆይ!***

ይህችን መንፈሳዊ መጽሔት ለማንበብ ባሉበት ጊዜ አሳብዎ ምን ያህል እንደተሰበሰበ አናውቅም። እኛ በዚህ ቁጥር ውስጥ ያሉትን መልእክቶች በምናዘጋጅበት ጊዜ በየዜና ማሰራጫው የምንሰማውና የምናየው የአሕዛብ መራወጥና የጦርነት ወሬ ልባችንን እየሰበረውና በብዙ የሚቆጠሩ ምንም ያልበደሉ ሰዎች ጥፋት ሞት እያሳዘነን ነው።

ምንም እንኳን ጌታ ራሱ «የጦር ወሬ ልትሰሙ ግድ አላችሁ» ብሎ አስቀድሞ በቃሉ ቢነግረንም፤ይህ የትንቢት ቃል ሲፈጸም ማየት ከተኛንበት መንፈሳዊ እንቅልፍ እንድንነቃ ይገፋፋናል።

ምናልባት የምንኖርበት አገር ከውጭው ሲታይ ሰላም የሰፈነበት የሚመስል ቢሆንም በውስጡ የመንፈስ መረበሽን የማያውቅ ሰው በጣም ጥቂት ነው። ቢሆንም ግን «ሰላሜን እተውላችሃለሁ፣ ሰላሜን አስጣችሃለሁ፣ እኔ የምሰጠው ሰላም አለም እንደሚሰጠው አይደለም። ልባችሁ አይጨነቅ ፣ አይፍራም» የሚለው የጌታ ተስፋ ቃል ዛሬም ይሠራል። ስለዚህ በዚህ ምድር ውስጥ ስንኖር የሰላም መስፍን የሆነው ክርስቶስ ልባችንን በሰማያዊ ሰላም እንዲሞላና በዙሪያችን ላሉት ሁሉ የሰላም መልእክተኛች እንዲያደርገን እንጠይቀው። «ሰላምን የሚያወርዱ ብጹአን ናቸው፤የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና»።

የተወደዱ አንባቢ ሆይ! ይህችን መጽሔት በሚያነቡበት ወቅት በጸሎት መንፈስ ተሞልተው በጦርነት ላይ እየተሰቃዩ ያሉትን ሰዎች እንዲያስቡ በትህትና እንጠይቅዎታለን። እኛም መልካሙን ነገር በሙሉ እየተመኘንልዎ «ሰላም ይሁንልዎ» እንላለን።

***የናንተው፥***

***ዳዊት መሐሪ እና ዳዊት መንግሥቱ***

# ወንጌል

## «ሞትን ልሞክረው»

አቦ አትጨቅጭቀኝ ይህን አርግ ያንን ተው
ይህንን ተመገብ ያንን አትቅመሰው
ይህ ነው የሕይወት መንገድ ያኛው ግን የሞት ነው
ያንተስ ተረት ተረት የት ይሆን ማለቂያው
በቃ አትጨቅጭቀኝ ሞትን ልሞክረው።»
ብሎ መለሰለት ዳኒ ለአለባቸው
እውነትና ሕይወት መንገድን ባሳየው።
«በቃ አትጨቅጭቀኝ ምክርህን ለራስህ
አንተም በያዝከው ሂድ ባንተ ማን መጣብህ
ደግሞ እኮ የሚገርመው በመጽሐፉም መሃል
ሁሉንም ፈትኑ ደጉን ያዙ ይላል።
እና በዚህ ዘመን ማነህ ተረዳኸኝ
አንድ ረዘም ያለ ትልቅ እቅድ አለኝ።
በቃ ሁሉን ማየት ...

ሁሉንም ማየት ነው ሁሉንም መፈተን
ፍልስፍናን ማንበብ መፈለግ ጥበብን
ሌት ተቀን ሳይሉ ክረምትና በጋ
እግር እስኪደክም ውበትን ፍለጋ
መዞር ነው አለምን በሃሳብ እና በአካል
በመንገድ እውነትን አገኘው ይሆናል።
ታዲያ ይህን ስልህ ዝም ብሎ አይደለም
መልካም የሚመስል የሚታለፍ የለም።
በተለይ በተለይ ጫትና ሲጋራ
የቀን ቀን ቪዲዮ የሌሊት ጭፈራ
ቀላል አይመቹም «ኢንጆይ» ታደርጋለህ
ነገር ግን እነዚህን ኃጢያት ናቸው ብለህ
የሕይወትና የሞት ሚኒስትር ይመስል
ይሄኛው ነው ሕይወት ያኛው ሞት ነው ብትል
ፍጹም አንስማማም በቃ ታቆማለህ
ደግሞ ለራሴ «ላይፍ» አንተ ምን አገባህ?
እንዲያውም እንዲገባህ ይኸን ሞት ነው ካልከው
በቃ አትጨቅጭቀኝ ሞትን ልሞክረው!»

አለና ዳኒ ቦይ እየተሳለቀ
እንዲያው በእርሱ ብሶ ራሱን ነቀነቀ።
ስለዚህ አለባቸው በጓደኛው አቋም
እጅግ በማዘኑ ልቡ ቢሰበርም
በመ/ቅዱስ በትንቢት ላይ ያለው
ክፋውን ነገር መልካም መልካሙን ክፉ ነው
የሚል ትውልድ አለ ብሎ የተነገረው
ወዲያው ትዝ ብሎት እየተገረመ
በቀጣዩ ግብዣ ሃሳቡን ፈጸመ።

«ወንድሜ ዳኒ ቦይ አስተውዬሃለሁ
ስለ ድምዳሜህ እጅጉን አዝናለሁ
ለመሆኑ...
ለመሆኑ እንዳንተ ሞትን ለመሞከር
በኦሎምፒክ መንደር ሪኮርድ በመስበር
አገሩን ያስጠራ ራሱን ያስከበረ
ምናልባት በታሪክ አንድ ሰው ነበረ?
እኔ ግን የማውቀው ...
እኔ ግን የማውቀው ሞትን በመሞከር
ወንጀልን በመስራት ሕዝብን በማስቸገር
ፖሊስ ጣቢያንና ወህኒን ያጣበቡ
አሊያም ጫትና ሲጋራ ሲስቡ
በልቅ ወሲብ መንደር «አለም ቀጨን» ሲሉ



ስብእናቸውን በኃጢያት የበከሉ
ዛሬ የሆስፒታልን ግማሽ አልጋ ይዘው
አዋጅ «እኔን ያየህ ተቀጣ» ሲሉ ነው።

ለማንኛውም ዳኒ የመጨረሻ ቃል
እራስን ማታለል እስካሁን ይበቃል።
እውን በሕይወቴ ትልቅ ግብ አለኝ ካልክ
እውነተኛ ደስታ እርካታን ከፈለክ
እውነትና ሕይወት መንገድ ኢየሱስ ነው
ሞትን ከመሞከር ሕይወትን ሞክረው!
ሞትን ከመሞከር ሕይወትን ሞክረው!

«ኑ እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱ እዩም»

«ሕዝቤ ሆይ ስማኝ እነግርሃለሁ
እስራኤል ሆይ ስማኝ እመሰክርልሃለሁ
አንተስ ብትሰማኝ ሌላ አምላክ
አይሆንልህም» (መዝ 81፥8-9) ◆

አትክልት ኢሳያስ
ከአ.አ. ዩኒቨርሲቲ

# ከአንባቢዎች

በጌታ ጸጋ እና በጎነት የአንድ አባት ልጆች ላደረገን ውድ የትንቢት ቃል አዘጋጆች፥- የእናንተን መጽሔት ተከታትሎ ለማንበብ እድሉ ባይኖረኝም ከእጄ የገባችው ቁጥር 3 ሶስተኛ ዓመት የምትለውን ነው። መጽሔታችሁን በማግኘቴ እጅግ ተደስቻለሁ፤በውስጧ ለተላለፈው ግሩም መልእክት ምክር ጌታ ይባርካችሁ። በተለይ እንደታሪክ ተደርጎ የቀረበው «ልጁና ምስማሩ» በልቤ ውስጥ እንዲታተም ሆኖአል። «የትንቢት ቃል» የሚለውን ለምን ተጠቀሙ? እያልኩ በዚህ ርእስ የሚታተሙትን ጽሑፎች ሁሉ የሚያመለክተው አስቀድሞ የተነገረው የትንቢት ቃል ዛሬ በዚህ ትውልድ መሀል ሲፈጸም ይበልጥ ራሳችንን በክብር ለሚገለጸው ንጉሥ እንድናዘጋጅ ያደፋፍረናል ብዬ አሰብኩ። ውድ አዘጋጆች ይህን በቃሉ ውስጥ ተጽፎ ያለውን የትንቢት ቃል እኔም ለወገኖች ለማስተላለፍ ቃል እየገባሁ እባካችሁ ከዚህ የበለጠ ምስክርነት የለምና ይህንን ጽሁፍ እንድትልኩልኝ በጌታ ስም እጠይቃችኋለሁ። ወንድማችሁ

ልኡልሰገድ ክፍሌ, ከከርፌ አደቬ.
ት/ቤ, ደብረ ዘይት

የተከበራችሁ የትንቢት ቃል አዘጋጆች፥- በየጊዜው የምትልኩልኝ መጽሔት ብዙ ትምህርትና በረከት ያለው ነው። አሁን ልጽፍላችሁ የፈለኩት በቅርቡ ስለተሠራችው ሕጻን ነው። መቸም በመጨረሻ ጊዜ የሰዎች እውቀት የላቀ እንደሚሆን ነው፣ነገር ግን የእግዚአብሔር ፍጥረትን የሚሻማ መሆን የለበትም ነው የምለው። ሰው ክቡር ፍጡር በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረ ስለ ሆነ ሰዎች ሲሠሩት ክብሩ ይቀንሳል እላለሁኝ። እንበልና ይህች ልጅ ብታድግ፤እኛ እንደምንለው አባባል «የፈጠርከኝ ጌታ እግዚአብሔር

*<u>በገጽ 4 ይቀጥላል</u>*

# መሰብሰባችንን አንተው

**ወንጌል በአሜሪካ**

## የኢትዮጵያውያን ሰባተኛ ቀን አክባሪ አድቬንቲስት ክርስቲያኖች አመታዊ ኮንፈረንስ በዋሺንግተን ዲሲ

መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ። ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህንን አድርጉ። (ዕብ 10፥25) የሚለውን የጌታን የፍጻሜ ዘመን ጥልቅ የምክር ቃል በማሰብ ከ 2000 ዓ.ም. ማለቂያ ጀምሮ ከጥቂት ወገኖች ጋር በስልክ በኢሜይል የተለያዩ ጽሑፎችን በመጻጻፍ የረዥም ጊዜ የሃሳብ ልውውጥና የተለየ የጾምና የጸሎት ጊዜን በመውሰድ በመወያየትና ራሳችንንም በማዘጋጀት በሰሜን አሜሪካ ያሉትን ኢትዮጵያዊያን አድቬንቲስቶች ለማበረታታትና ሌሎች ነፍሳትንም በወንጌል እውነት ለመድረስ የሚጠበቅብንን ቅዱስና ክቡር ኃላፊነት መወጣት እንዳለብን በየጊዜው ከጥቂት ወገኖች ጋር እለት ከእለት ሲከብደን የነበረ ጉዳይ ነበር።

የየግል ድካማችንን ያለማቋረጥ በመስቀሉ ስር በመጣል፣የመስቀሉን ቃል ባለመቀበል ያልዳኑትን ወደ መስቀሉ በማመላከት በመበርታት ላይ ያሉት በዚያው እንዲቀጥሉ፣የደከሙት እንዲበረቱና ከጌታ ቤት የጠፉት ደግሞ ወደ መንጋው በረት እንዲመለሱ፣እውነትን አግኝተው ያልዳኑት እውነትን በጌታችን በየሱስ ክርስቶስ ንጹህ ወንጌል መሠረት እንዲያውቁ በማለት እሮብ ጁላይ 3 እስከ ቅዳሜ ማታ ጁላይ 6, 2002 ድረስ በዋሺንግተን ዲሲ በካፒታል ሚሞሪያል አድቬንቲስት ቤ/ክ ውስጥ ለጥቂት አመታት ተቋርጦ የነበረው አመታዊ ኮንፈረንስ ጅምሩና ማለቂያው እጅግ አስደሳችና ብዙ በረከት የሞላበት ስብሰባ ተጀመረ። ኮንፈረንሱን 12 ሰዎች የምንሆን በጸሎት በመጀመር ለትውውቅ ጊዜ ከወሰድን በኋላ ጌታን በዝማሬ በማመስገን ቀጠልን። ከጌታ ቃል ከእለቱ አገልጋይ ከሰማን በኋላ የምሽቱን ስብሰባችንን በማጠናቀቅ ወደየማረፊያ ስፍራችን ሄድን።

በሚቀጥለው ቀን ሐሙስ ጥዋት ከጥዋቱ 4 ሰዓት በመገናኘት ስብሰባችንን ቀጠልን። የስብሰባውም ዋና አላማና ርእስ የክርስትና ሕይወታችንን እንዴት ማጠናከር እንደምንችል ነበር። የተለያዩ ወገኖች ከተለያዩ የአሜሪካን ክፍለ አገሮች እና ወንድማችን ዳዊት መሐሪ ከጀርመን በመካከላችን በመገኘት በአንድ አላማና በአንድ መንፈስ አስደሳች የሆነ ፍቅር እና አንድነት በሞላበት በጸሎት



በተሞላ አንድነትና ህብረት ስብሰባችን በየቀኑ ይቀጥል ነበር። ለእያንዳንዱ ተናጋሪ የአንድ ሰዓት ጊዜ ተሰጥቶት ነበር። የጠዋት የከሰአትና የማታ ፕሮግራም ነበረን። በየፕሮግራሙ መካከል በሌላ ክፍል ውስጥ ሁነው በጸሎት የሚጋደሉ ወገኖችም ነበሩን። ከዚህም ባሻገር በስብሰባችን መሃል የምስክርነት ጊዜ የግልና የግሩፕ የዝማሬ ጊዜ እንዲሁም የተለየ የጸሎት ጊዜም ከጉባኤው ጋር ነበረን። በዚህ ሁሉ ውስጥ ጌታ በየእለቱ ወደ ስብሰባው የሚመጡትን ነፍሳት ይጨምር ነበር። እለት በእለት ቁጥራችን እየበዛ ሄደ። አርብ እለት ወደ 45 የሚሆኑ ሰዎች ነበሩ። ቅዳሜ ሰንበት ቀን ከ 70 በላይ በሚሆኑ ሰዎች ወደ ስብሰባችን ማጠናቀቅ ሰዓት እየተቃረብን መጣን።

አገልጋዮች በአጠቃላይ አብዛኛዎቻችን ከዲሲ ውጪ የመጣን፣እጅግ ሕይወትን የሚነካ የወንድማማች ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስን ሥራና እውነተኛ የሆነ የልብ አንድነትን አይተናል ስንል ማጋነናችን አይደለም። በመጨረሻም ሰፋ ያለ የውይይት ጊዜ ከጉባኤው ጋር እና በግልም ልዩ ልዩ ጥያቄ ካላቸው ጋር ካደረግን በኋላ ይህ አመታዊ ኮንፈረንስ በየአመቱ እንዲቀጥል ተስማምተን፤በዲሲ የሚገኙ ወንድሞችና እህቶች ወደፊት በየሳምንቱም የመሰብሰብ አላማ እንዳላቸው ከገለጹልን በኋላ የስብሰባውን ተሳታፊዎች ስምና አድራሻ ከሰጡን ሁሉ በመውሰድ፤እስከሚቀጥለው የስብሰባችን ጊዜ ድረስ በሚገባ እንደምንጠያየቅ፣በጸሑፍና በስልክም እንደአስፈላጊነቱ እንደምንደርስላቸው በየግል ጸሎታችንም አጥብቀን እንደምናስባቸው ገልጸንላቸው ስብሰባችንን በዝማሬ በምስጋናና በጸሎት በማገባደድ እነርሱንና እኛን ለጌታና ለጸጋው ቃል አደራ ሰጥተን በዚህ አለም ውስጥ እስካለን ድረስ ሁላችንም የተለያየ የመኖሪያ ስፍራ አለንና ወደየመጣንበት አቅጣጫ በልዩ ናፍቆትና ትዝታ በጌታ በረከት ተባርከንና ተሞልተን ሁላችንም በሰላም ተመለስን። ክብር ሁሉ ለጌታ ይሁን።

በአለም ዙሪያ ለተበተናችሁት ወገኖች አደራ የምንላችሁ በተለይ በዚህ ስፍራ ላለን «ወንድሞች ስለ እኛ ጸልዩ» (1ተሰ5፥25)። በተለየ መንገድ ጸልዩልን ትልቅ ውጊያ ያለበት ምድር ነውና የምንገኘው። በነገር ሁሉ ጌታ ሁላችንንም ያበርታን ይባርከንም፣ለማታልፈውም ዘላለማዊት አገራችን ያብቃን። ጌታ ይባርካችሁ።◆

በጌታ የፍጻሜ ወንድማችሁ ታሪኩ አዩ፣ ከደቡብ ካሊፎርኒያ

***«የሰንበትን ቀን አስብ...» (ከገጽ1 የዞረ)***

ኢትዮጵያ ላከች። ከመልእክተኞቹ መካከል አንዱ «አልባሬዝ» በዚያ ዘመን የኢትዮጵያ ንጉሥ የነበረውን ልብነ ድንግልንና የአቡነውን እምነት (ድጋፍ) አገኘ። እንዲያውም ሰንበትና የሙሴ የምግብ ሕግ (ስለሚፈቀዱትና ስለማይፈቀዱት ምግቦች) እንዴት መወገድ እንደሚችሉ ተወያዩ። ከ6 ዓመት በኋላ የፖርቱጋል መሪዎች ወደ አገራቸው ሲመለሱ «ዛጋ ዛቦ» የተባለውን የኢትዮጵያ መልእክተኛ ይዘው ሄዱ። ይህም መልእክተኛ ኢትዮጵያውያኖች ሰንበትን ለምን እንደሚያከብሩ የሚከተለውን ምክንያት ሰጠ፥-

«እግዚአብሔር ዓለምን ፈጥሮ በ 7ኛው ቀን ስላረፈ እና ይህንን ቀን ቅዱስ ስላለው፣ይህንን ቀን አለማክበር ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ የሚጸናውን የእግዚአብሔርን ፈቃድና ትእዛዝ ይቃረናል። ምክንያቱም ክርስቶስ የመጣው ሕግን ለመሻር ሳይሆን ለመፈጸም ነው። ስለዚህ ሰንበትን መጠበቃችን አይሁዶችን ለመከተል (ለመኮረጅ) ሳይሆን ክርስቶስንና የሐዋሪያትን ትምህርት ለመታዘዝ ነው» (ዋቢ፥ Gustav Tobler, pp. 181,182)

ይህ በእንዲህ እያለ በግራኝ መሐመድ የተመራው የእስልምና የማጥቃት እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ብዙ ጥፋትን አስከተለ። ንጉሥ ልብነ ድንግል ተስፋ ከመቁረጡ የተነሳ በ1535 ዓ.ም. የአውሮፓን እርዳታ ለመነ። እንዲያውም የፖርቱጋሎችን እርዳታ ለማግኘት ሲል ለሮም ቤ/ክ ለመገዛት ፈቃደኛ እንደሆነ እንዲህ በማለት ገለጸ፥- «እምነታችንንና ቤተክርስቲያናችንን በሮም ቤ/ክ ስር እንድትሆን ለማድረግ ፣ ፖርቱጋልም በእኛ ላይ እንድትነግስ ፈቃደኞች ነን። እኛ እና ህዝባችን የፖርቱጋልና በሮም ካቶሊክ ቤ/ክ ስር ለመሆን ፈቃደኛነታችንን እንገልጻለን።» (ዋቢ፥- Tekletsadik Mekuria, A History of Ethiopia from Lebna Dengel to Tewodros, 1953, pp. 194,195)

የልብነ ድንግል ተከታይ ገላውዲዮስ በ1541 ዓ.ም. ከፖርቱጋል በተላኩት 400 ወታደሮች አማካኝነት የእስላም ጠላቶቹንና ግራኝ መሐመድን ድል ሊነሳ ቻለ። ከዚህ ድል በኋላ ግን ንጉሥ ገላውዲዮስ ያባቱን ቃል በማጠፍ ለሮም ቤ/ክ እንደማይገዛ ተናገረ። ዳዳስ ዩሊዮስ 3ኛው የሱኢቶችን (Jesuits) በመላክ የንጉሡን ሃሳብ ለማስቀረት ሞከረ። እንዲያውም ለኢትዮጵያ ቤ/ክ መሪ እንዲሆን አንድ ዳዳስ (አቡነ) ሾመ። ንጉሡ ገላውዲዮስ የዳዳሱን መልእክተኞች በትህትና ቢያስተናግዳቸውም የሮም ግብዣን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑን ገለጸ። ለዚህ ያቀረበውም ምክንያት ያባቶቹን እምነት ለማጽናት መፈለጉን ነው።

ለኢትዮጵያውያን ሰንበትን ማክበር በጣም ወሳኝ ከመሆኑ የተነሳ «ዘድንግል» የተባለው የኢትዮጵያ ንጉሥ «ማንም ሰው ሰንበትን ቅዱስ ቀን ነው ብሎ ሊጠብቅ አይፈቀድለትም!» ብሎ አዋጅ ሲያወጣ ሕዝቡ ወዲያውኑ ከስልጣኑ አስወገዱት። ይህንን አዋጅ በድፍረት ለማወጅ የበቃው ከጥቂት ጊዜ በፊት ከስፔይን አገር በመጣው የሱኢት «ፔሮ ፓኤዝ»

***በገጽ 4 ይቀጥላል***



## ጤናችን

# የአካል እንቅስቃሴ ጥቅም

አካልን ማለማመድ (ስፖርት፣እንቅስቃሴ) በጤንነት ላይ ይህ ነው የማይባል ታላቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ይታወቃል። ለምሳሌ በየቀኑ ለ 20 ደቂቃ በእግር ሽርሽር የሚሄዱ ሰዎች እንቅልፍ በማጣት የመቸገራቸው እድል ከማይንቀሳቀሱቱ ጋር ሲነጻጸር በ 33% ያነሰ ነው። የአካል እንቅስቃሴ ለልብ ሥራና ለደም ስሮች ጤንነትም በጣም ወሳኝ ነው።




የአካል እንቅስቃሴ (ልምምድ) የደም ስሮችን የመለጠጥ ችሎታ እንዲጨምርና ከፍ ያለ የደም ግፊት (ብዛት) እንዲቀንስ ከማድረጉም በላይ፤በደም ውስጥ ያለ የቅባት መጠን ዝቅ እንዲል ይረዳል። በተጨማሪም የአካልን ጡንቻዎች ማለማመድ እያንዳንዱ ሴል በቂ ንጹህ አየርንና ንጥረ ነገሮችን እንዲያገኝ ያደርጋል።

አካላቸውን የማያለማምዱ ሰዎች በሽታን የመከላከል ኃይላቸው በጣም ዝቅ ያለ ከመሆኑ የተነሳ በኢንፌክሺን በቀላሉ ይጠቃሉ። ያልተጋነነ ስፖርት ከተስተካከለ አመጋገብ ጋር የአካል መደበኛ ኪሎ እንዲጠበቅ ስለሚረዳ አብዛኞቹን ከውፍረት ጋር ሊያያዙ የሚችሉትን በሽታዎች (ለምሳሌ፥ የደም ብዛት፣ የስኳር በሽታ ወዘተ.) ለመከላከልና ለማዳን መንገድን ይከፍታል።

«እንቅስቃሴ ሕይወት ነው» ይባላል። ስለዚህ ፈጣሪ የሰጠንን ድንቅ አካል በትክክል በመጠቀም ራሳችንን በጤንነት እንጠብቅ ዘንድ የሰማይ አባታችን ፍላጎት ነው።◆

አዘጋጆች

*<u>ከአንባቢዎች</u>* *(ከገጽ 2 የዞረ)*

በሰላም አውለኸኝ አለህና በሰላም አሳድረኝ» ለማለት እንኳን የምትደፍር አይመስለኝም ፤ምክንያቱም የልጅቷ ታሪክ አንድ ጊዜ ለራሷ ይነገራታል፤ማን እንደሠራት። ሌላ ደግሞ ከሞት በኋላ ያለው ነገር ስለ ልጅቷ ያሳስበኛል። በሰዎች እውቀት ስለተሠራች፤ማለት ሰው ሸክላ እንስራ እንደሚሠራ ማለት ነው ቢሰበር ገል ሁኖ ይቀራል፤ብትሞት እጣዋ ምንድን ነው የሚሆነው? ብዬ አስባለሁኝ። ለጥሞና ጊዜ እንዲረዳ ያወጣችሁት ካሌንደር መልካም መመሪያ ነው። በየእለቱ በማስታወስ የሚነበብ። በ3 ወር ውስጥ 10000 ነፍሳት ወደ ጌታ መምጣታቸውም አስደሳች ዜና ነው። እምነታቸውን እንዲያጸናላቸውና በሚያደርጉት መልካም ነገር እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር እንዲሆን ምኞቴ ነው። የጌታ ኢየሱስ ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን።◆

ግምጃ አማረ መዓሾ, ከአስመራ

*<u>«የሰንበትን ቀን አስብ...»</u>* *(ከገጽ 3 የዞረ)*

አማካኝነት የካቶሊክን እምነት ከተቀበለ በኋላ ነበር። በዚያን ዘመን የሕዝቡ ተቃውሞ በጣም አስከፊ ነበር። አቡነው ሕዝቡን ለንጉሡ ከነበረው ታማኝነት (መገዛት) ነጻ አወጣው። ታላቅም ረብሻ ተነሳ። ረብሻው አስከፊ ከመሆኑ የተነሳ በዚህ ሽብር ጊዜ ለንጉሡ 200 የፖርቱጋል ወታደሮች ቢዋጉለትም በመጨረሻ ተገደለ። ከንጉሥ ዘድንግል በኋላም ሰንበትን ለማስወገድ የሞከሩት መሪዎችም ሳይሳካላቸው ቀረ። (ዋቢ፥- Hammerschmidt, pg. 56)

<u>የሰንበት ጥያቄ በኢትዮጵያ በ17ኛው ክ/ዘ</u>

ኢትዮጵያን ካቶሊክ የማድረግና ሰንበትን የማስወገድ ጥረት በ1617 ዓ.ም. ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት በቀየረው በንጉሥ ሱሴንዮስ ዘመን ሆነ (1607-1632)። ይህ ንጉሥ ከሱ በታች የሆኑት ሁሉ እምነታቸውን ወደ ሮማ ቤ/ክ እንዲለውጡ አዋጅ አወጣ። በ1620 ዓ.ም. ሰንበትን በሚጠብቁት ላይ አስከፊ ቅጣት እንደሚያደርስባቸው አስጠነቀቀ። እሁድ የጌታ ቀን ስለሆነ እንዲከበር ትእዛዝ አወጣ፤ይህንን ትእዛዝ በማያከብሩትም አስከፊ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው አስታወቀ። የሮማ ቤ/ክ የንጉሡን እቅድ በመደገፍ በርከት ያሉ የሱኢቶችን ላኩለት። እነርሱም በሰንበት ቀን እርሻ ላይ በማይሰማሩት ገበሬዎች ላይ ታላቅ የተቃውሞ ግፊት አደረሱባቸው (ዋቢ፥- Hammerschmidt, pg. 56)። በተጨማሪም «አልፎንዞ ሜንዴዝ» የተባለውን ሰው የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ እንዲሆን አድርጎ በመሾም እሱ ንጉሥ ሱሴንዮስን፣ ልጆቹንና አገልጋዮቹን በሮማ ጳጳስ ስር ለመሆን ፈቃደኞች መሆናቸውን እንደገና አስማሉአቸው። ነገር ግን ይህ የኢትዮጵያ ንጉሥና የሮማ ቤ/ክ ህብረት በኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅ ተቃውሞን አስከተለ። በመጀመሪያ ጥቂት ተቃዋሚዎች ሲነሱ እነርሱን ንጉሡ አቆማቸው። የተቃውሞው እንቅስቃሴ ግን እየተስፋፋ ሄደ፥-

«ይህ እንደነገሩ የተጀመረው ለውጥ በንጉሡ ላይ አስከፊ ተቃውሞ አደረሰ። እየተስፋፋ የመጣው ተቃውሞ አገሪቷን ወደሚጎዳው ወደ ሃይማኖት ጦርነት እንዲያመራ አስገደደው ... ንጉሡ ሱሴንዮስ ተቃዋሚዎቹን በጦርነት ድል እየነሳ ሳለ በልጁ ፋሲለደስ እና በሌሎች ተጽእኖ አማካኝነት የሕዝቡን እልቂት እንዲያቆም ተገደደ፤ከዚያም በሰኔ ወር 1632 ዓ.ም. የሃይማኖትን ነጻነት አወጀ» (ዋቢ፥- Vyhmeister, pg. 184)



ሰንበትን በኢትዮጵያ የማስወገድና አገሪቷን ወደ ካቶሊክ የመለወጥ ቁርጥ ሙከራ በዚህ አበቃ። ኤርንስት ሐመርሽሚት ስለዚህ ጉዳይ ሲጽፍ፥- «ታሪክን ከሩቅ ሆነን ስንመለከት የንጉሥ ሱሴንዮስ እና የአልፎንዞ ሜንዴዝ የህብረት ሙከራ ውጤት እንደማይኖረው ግልጽ ነበር፤ምክንያቱም ሰንበት ለአንድ ኢትዮጵያዊ በቀላሉ ሊክደው የማይችለው ጉዳይ ነበርና» (ዋቢ፥- Hammerschmidt, pg. 57)።

ከዚያም የ ሱሴንዮስ አልጋወራሽ የነበረው ንጉሥ ፋሲለደስ በአገሩ ውስጥ የነበሩትን የሱኢቶች በሙሉ ከአገሩ አስወጣ። በወቅቱ ያገኛቸውንም የካቶሊክ መጽሐፍቶች በሙሉ አቃጠለ። ከየሱኢቶችም ጋር ተባብረው የነበሩትንም ቄሶች በሙሉ ገደለ (ዋቢ፥- Werner Vyhmeister, „The Sabbath in Scripture and History“, pp.180-184)።

<u>... ዛሬስ?</u>

ዛሬ የሰንበት ጥያቄ በጣም ተለውጦአል። ክርስቲያኖች «ሰንበትን እናከብራለን» ብለው ሲናገሩ ለአንዳንድ ኢትዮጵያውያን ጆሮ እንግዳ እና እንደሚያስደንቅ ነገር ሆኖ ነው የሚታየው። ታሪክ ሲዘነጋ (ሲረሳ) ውጤቱ ይህ ነው። ሙሴ እግዚአብሔርን በግብጽ ሰለተጨቆነው ሕዝብ ሲጠይቀው እንደዚሁ ነበር፥- «...የአባቶቻችሁ አምላክ ወደ እናንተ ላከኝ ባልሁም ጊዜ፤ስሙስ ማን ነው? ባሉኝ ጊዜ ምን እላቸዋለሁ?» (ዘጸ 3፥13)። ሕዝቡ አምላኩን ረስቶ ነበር። በግብጽ አገር ብዙ ሥራ ነበራቸውና። እኛንም እንደባርነት የያዘን ብዙ ሥራ አለን። ባለፈው ክ/ዘ ይኖር የነበረ አንድ ኢትዮጵያዊ ክርስቲያን በቅዳሜ ሰንበት በመርካቶ የሚደረገውን ገበያ ቢመለከት በጣም ያዝን ነበር። እኛ ግን ምንም አይመስለንም። ያልተለመደው የተለመደ ሲሆንና እውነት እንደ ብርቅ ሲሆን ውጤቱ እንዲህ ነው።

<u>የአባቶቻችን እምነት</u>

ከመጽሐፍ ቅዱስ ለወረሱት እውነት ጸንተው በመቆም አባቶቻችን ስላሳዩት እምነት ልናደንቃቸው ይገባል። ይህ የሚያሳየው እውነት ለነርሱ ከሕይወታቸው የበለጠ ወሳኝ ነገር እንደሆነ ነው። እኛ ዛሬ ሃይማኖተኛነታችንን ከእለታዊ ኑሮአችን ለይተን (ነጥለን) ነው የምንመለከተው። *<u>በገጽ 5 ይቀጥላል</u>*

## ተከታታይ ትምህርት



## የሎዶቅያ ቤ/ክ

(አስቀድመው በዮሐንስ ራእይ ምእራፍ 3፥14-22 ያለውን ያንብቡ!)

የሎዶቂያ ቤ/ክ ከሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የመጨረሻዋ ናት። ሌላ ስምንተኛ ቤ/ክ የለም። የሰው ልጆች ታሪክም የሚያልቀው በዚህች የሎዶቂያ ቤ/ክ ታሪክ ጊዜ ነው። «ሎዶቂያ» ማለት ትርጉሙ «የፍርድ ሕዝብ» ማለት ነው። በፊላደልፊያ ቤ/ክ ወቅት ወደ ፍርድ ሰዓት እንደገባን ሁሉ የሎዶቂያ ቤ/ክ ደግሞ ወደተጀመረው ፍርድ ፍጻሜ ታመጣናለች። ይህም በ1800 ዓመተ ምህረቶቹ መካከል ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጊዜ ያለውን ያጠቃልላል። ስለዚህ የሎዶቂያ መልእክት ከሌሎቹ ከስድስቱ ይበልጥ በአሁኑ ወቅት ያለችውን ቤ/ክ ያመለክታል።

**አሰቃቂ በሽታ**

ያለፉት ስድስት መልእክቶች የወቀሳና የሙገሣ ነበሩ። የሎዶቂያ ግን የተለየ ነው። የሱስ የሎዶቂያ ቤ/ክ ስላለችበት ወቅታዊ ሁኔታ ምንም የሚናገረው መልካም ነገር የለም። ቢሆንም ግን መልእክቱ በአጠቃላይ እሰከፊ አይደለም። ክርስቶስ ሎዶቂያ ታላቅ የመፈወስ ተስፋ እንዳላት ያመለክታል። ይህም እውነተኛ ፈውስ ሲሆን የከበረው ተስፋ ደግሞ ድል ለነሱቱ ይሆናል።

«ትኩስ መሆን» ማለት ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ መገዛት፣በእምነት መጠንከር፣በፍቅር ታማኝ መሆንና ለአገልግሎት ራስን መሰዋት ማለት ሲሆን፤«ቀዝቃዛ መሆን» ማለት ደግሞ በግልጽና በማወቅ ራስን ከክርስቶስ መለየት ማለት ነው። ሎዶቂያ ወይ ትኩስ ወይ ቀዝቃዛ አይደለችም። ወይ ሙሉ በሙሉ ራስዋን ለየሱስ አልሰጠችም ወይንም ሙሉ በሙሉ አልካደችውም። ብቻ «ለብ» ያለች ናት። በግማሽ ልብ በመንፈስ የእንቅልፍ ሰመመን ውስጥ ናት። የሎዶቂያን ሁኔታ ከሚያባብሱት ነጥቦች ውስጥ አንዱ ያለችበት ሁኔታ ምን አይነት እንደሆነ አለማወቅዋ ነው። ሁኔታዋን አለማወቅዋ ብቻ ሳይሆን ራስዋን በመንፈስ ባለጸጋ እና ምንም እንደማያስፈልጋት በመቁጠር ራስዋን ማታለልዋ ነው። ሐቁ ግን «ጎስቋላ፣ድሃ፣እውርና እርቃንዋ የሚታይ» ናት። ሎዶቂያ ጽኑ በሽተኛ ከመሆንዋ የተነሳ ክርስቶስ «ሁኔታሽ እኔንም ያሳምመኛል፣ከአፌ አውጥቼ እተፋሻለሁ!» ይላታል። የሱስ ለቤተክርስቲያኑ ያለው ፍቅር ታላቅ ከመሆኑ የተነሳ ነው ይህንን አይነት ኃይለኛ ወቀሳ የላከላት። «የምወደውን ሁሉ እገስጸዋለሁ» ይላል። ለችግሯ በቀጥታ የሚሰጣት መፍትሔ (ፈውስ) የሚያሳየው ፍቅሩንና ጥንቃቄውን ነው እንጂ ለዘላለም እንደሚተዋት አይደለም።

**እውነተኛ ፈውስ**

ታማኙና እውነተኛው ምስክር የሚነግረን ያለንበትን ሁኔታ ብቻ ሳይሆን፤የሚሰጠንም ፈውስ የሚስተካከለው የሌለ ነው። በመጀመሪያ «በእሳት የነጠረው ወርቅ ያስፈልጋችኋል» ይለናል። ሐዋሪያው ጴጥሮስ ይህ አይነቱ መንፈሳዊ ሃብት «የተፈተነ እምነት» እንደሆነ ያስረዳል (1ጴጥ1፥6-9 ይመልከቱ)። ጳውሎስም «በፍቅር የሚሰራ እምነት» ይላል (ገላ5፥6)። ይህም የክርስቶስ ፍቅር በፈተና ጊዜ ውስጥ በእምነት እንድንጸና የሚያደፋፍረን ኃይል እንደሆነ ያሳያል። በእሳት ውስጥ የተፈተነ ወርቅ ከፍቅር የተነሳ የሚጸና እምነት ነው ማለት ነው።

ሁለተኛው የፈውስ መንገድ ደግሞ «ነጭ ልብስ» መልበስ ነው (ራእይ 3፥18)። በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ አለፍ ብለን ስናነብ ደግሞ ይህ ነጭ ልብስ «የቅዱሳን ጽድቅ» እንደሆነ እናያለን (ራእይ 19፥8)። ይህንን ነጥብ በትክክሉ ልንረዳው ያስፈልጋል። ይህ ጽድቅ ቅዱሳን በራሳቸው ሥራና ጥረት የሚያገኙት ጽድቅ አይደለም። ከ24ቱ ሽማግሌዎች አንዱ ለዮሐንስ ሲያስረዳው «እነዚህ ልብሳቸውን በበጉ ደም አጥበው አነጹ» ይላል (ራእይ 7፥14)። በሰማይ አባታችን ፊት እንድንቀርብ የሚያስችለን የክርስቶስ ደም ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ የሱስ ደም የሚናገረው እሱ ራሱ በፈቃደኝነት ለእኛ ደህንነት ሲል ራሱን መሰዋቱ ነው። እኛም ነጭ ልብስ መቀበል የምንችለው ይህ የፍቅር መስዋእትነት ልባችን ውስጥ ሰርጎ እንዲገባና በውስጣችን የተሰበረ እና ትሁት ልብ እንዲፈጥር ለጌታ ስንፈቅድ ብቻ ነው። እንደዚህ አይነቱ መለኮታዊ ፍቅር ኩራትንና በራስ ሥራ መመካትን ያስወግድልናል።

ሶስተኛውና የመጨረሻው የፈውስ መድኃኒት ደግሞ «የአይን ኩል» ነው። ይህ መድኃኒት የሱስ ሎዶቂያን ለወቀሰበት የእውርነት በሽታ ገጣሚ መድኃኒት ነው። የሎዶቂያ ቤ/ክ ክርስቶስ በሚያየት አይን ራስዋን ማየት ይኖርባታል። በዚህም መንገድ ነው ያለችበትን አደገኛ የሆነ ሁኔታ መገንዘብ የምትችለው። ልብዋና አእምሮዋ የእግዚአብሔርን ድምጽ ለመስማት ዘወትር ዝግጁ መሆን አለበት።

አይንን በኩል መኳል ማለት፤መንፈሳዊነት የሚታደስበትና አእምሮ የሚነቃበት መንገድ ነው። የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎትም ከዚህ ምሳሌ ጋር ይዛመዳል (ዮሐ 16፥8,13 እና ኢሳ 11፥2,3 ይመልከቱ)። መንፈስ ቅዱስ በሰው አእምሮ ላይ በመሥራት መንፈሳዊ እውቀት እንዲዳብርና መንፈሳዊ አይኖቻችን ነገሮችን ማስተዋል እንዲችሉ ያደርጋል። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠቀምበት ዋናው መሳሪያው «የመንፈስ ሰይፍ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ነው» (ኤፌ 6፥17)

**እያንኳኳ ነው**

ጌታችን ሁኔታችንን በሚመለከት ጉዳይ ላይ ወቀሳው ግልጽ እና ቀጥተኛ ቢሆንም አነጋገሩ ትህትና የተሞላ ነው፦ «እነሆ በደጅ [በልብህ] ቆሜ [በትእግስት እጠብቃለሁ] አንኳኳለሁ [እንድታዳምጠኝ እማጸናለሁ] ማንም ሰው [ልዩነት የለም] ድምጼን ቢሰማ [ቢያስተውል] ደጁንም ቢከፍትልኝ [ከውስጥ በኩል] እኔም እገባለሁ [ያለምንም ማወላወል] ወደ እርሱ [ወደ ልቡ]፤ከእርሱም ጋራ እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል [መንፈሳዊ ሕብረት ይኖረናል]። (ራእይ 3፥20 ፤ በቅንፍ ያሉት ቃላት ሃሳቡን ለማጉላት የተጨመሩ ናቸው)።

**የአሸናፊው ሽልማት**

ወደ ሰው ልጅ ታሪክ መደምደሚያ የምታደርሰን የሰባተኛዪቱ ቤ/ክ ጥሪ ልዩ እንደመሆኑ መጠን ለመጨረሻው ዘመን ድል ነሺዎች የተሰጠውም ተስፋም እንዲሁ ልዩ ነው። ይህ ሽልማት በለስላሳ ድምጽ ጀምሮ በሚያስተጋባ ዜማ የሚያልቅን ሙዚቃ ይመስላል። የአሸናፊው ሽልማት በቀትር ቦግ ብሎ እንደሚያበራ የፀሐይ ብርሃን ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሰው ልጆች ከተሰጡትም ክቡር ተስፋዎች ሁሉ የላቀ ነው። የዘላለም ሕይወት ተስፋ፣የአዲሲቱ ምድር ተስፋና ከክርስቶስ ጋር ለዘላለም የሚኖረን መንፈሳዊ ሕብረት አይበቃ ይመስል፤ከዚህ ሁሉ በላይ ከእሱ ጋር አብረን ዙፋኑ ላይ እንድንቀመጥ ይጋብዘናል (ራእይ 3፥21)። አንባቢ ሆይ! ይህ ምን ማለት እንደሆነ መገመት ይችላሉን? በኃጥያት የወደቁ አመጸኞች ሰዎች የደህንነትን ስጦታ ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ የመቀመጥን ክብር ሲያገኙ! እስቲ ራስዎትን ነቅንቀው፣አይንዎችዎን አሻሽተው ይህንን ጥቅስ ደግመው ደግመው ያንብቡት! ደግመው ደጋግመው ባነበቡ ቁጥር ይህ እውነት ሐቅ ከመሆኑ የተነሳ የበለጠ ያስገርምዎታል።

«ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጣል» ሲል የሱስ፤ድል የነሱት ሁሉ በጣም ትልቅ በሆነ ዙፋን ላይ ቃል በቃል ከኔ ጋር ይቀመጣሉ ማለቱ አይደለም። ዙፋን የእግዚአብሔር ስልጣን የሚመነጭበትና መንግሥቱን (ግዛቱን) ሁሉ በስርአት የሚያስተዳድርበት ስፍራ ነው። በዚህ መሠረት ዙፋኑን የመካፈል ተስፋ፣አለማትን በሙሉ ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ የማስተዳደር ልዩ ተስፋ እንደሆነ እናያለን።◆



የራእይ መጽሐፍ ይናገራል
ትርጉም በታምሬ አባተ

**«የሰንበትን ቀን አስብ...» (ከገጽ 4 የዞረ)**

እንኳን ሕይወታችንን ይቅርና ሥራችንን እንኳን ለጌታ ሰንበት ብለን አሳልፈን ለመስጠት ፈቃደኞች አይደለንም። ለጌታው ታማኝ የሆነ የክርስትና ሕይወት መስዋእትነትን ይጠይቃል። አንድ ክርስቲያን ሰንበትን ሲያከብር እግዚአብሔር እንደተቀበለውና እንዳዳነው ያሳያል። ለተገለጠለት ለዚህ አስደናቂ ፍቅር ምላሹን ከአዳኙ ጋር ጊዜን በመውሰድ (በማሳለፍ) ግንኙነቱን ያጠነክራል። ይህ መስዋእትነት ነው? አዎን! ምክንያቱም ይህ መስዋእትነት ክርስቲያኑ የሕይወት ትርጉም ምን እንደሆነ እንዲያስተውል ያደርገዋል። በዚያን ቀን ከጌታው ጋር በሚወስደው የጥሞና ጊዜ ይህ ክርስቲያን እሱ ማን እንደሆነና ለምን እንደተፈጠረ በጥልቅ እየተረዳ እንዲመጣ ያደርገዋል።

አባቶቻችን ላመኑበት ነገር ህይወታቸውን አሳልፈው ሰጡ። አንተስ ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ ከአንተ ጋር ቀጠሮ ለያዘው ፈጣሪ ምን አይነት መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ ነህ?◆

ስምረት መሐሪ (ጀርመን)





# መጠበቂያው የእግዚአብሔር ቃል

## ከታላቁ ተጋድሎ ምእራፍ 37

መደ ሕጉና መደ ምስክር ቃሉ ሂዱ! እነርሱም እንዲህ ያለውን ቃል ባይናገሩ የንጋት ብርሃን አይበራላቸውም» (ኢሳ. 8፥20)

የእግዚአብሔር ሕዝቦች በሐሰት መምህራን ትምህርትና በጨለማ መናፍስት አታላይ ኃይል እንዳይሳቡ (እንዳይታለሉ) ጠባቂያቸው ወደሆነው ወደ እግዚአብሔር ቃል ይመራሉ። ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስን እውቀት እንዳያገኙ ለመከላከል ሰይጣን በተቻለው ብልሃት ሁሉ ይጠቀማል። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የሱን የማታለል ሥራ ስለሚያጋልጥበት ነው። በማንኛቸውም የእግዚአብሔር ሥራ በተሃድሶ ወቅት የክፋት ልዑል ደግሞ በእንቅስቃሴው ይበልጥ የተጋ ይሆናል። በአሁኑ ወቅት ሰይጣን ክርስቶስንና ተከታዮቹን በመቃወም የሚያደርገውን የመጨረሻ ትግል ለማካሄድ የሚቻለውን ጥረት እያደረገ ነው። ታላቁና የመጨረሻው የማታለል ሥራው በቅርቡ በፊታችን ሊገለጥ (ሊታይ) ነው። የክርስቶስ ተቃዋሚ በአይናችን ፊት ድንቅ ሥራውን ሊያከናውን ነው። በእውነትና በአስመሳይ እውነት መካከል ያለው ልዩነት በጣም ከመመሳሰላቸው የተነሳ በመጽሐፍ ቅዱስ ካልሆነ በስተቀር መለይት አይቻልም። ማንኛውም ምስክርነትና ማንኛውም ተአምር በቅዱሱ ቃል መለካት (መፈተን) ይኖርበታል።

የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ለመፈጸም የሚሞክሩ ሁሉ ተቃውሞ ያጋጥማቸዋል፤ሰዎችም ይሳለቁባቸዋል። እነርሱ መቆም የሚችሉት በእግዚአብሔር ብቻ ነው። የሚጠብቃቸውንም ፈተና ለመቋቋም እንዲችሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ አለባቸው። እርሱን ሊያከብሩና ፈቃዱን ለማድረግ የሚችሉት ስለ ባህርዩ፣ስለ መንግሥቱና ስለ አላማው ትክክለኛ ግንዛቤ ሲኖራቸው ብቻ ነው። በመጨረሻው ታልቁ ተጋድሎ ወቅት ሊቆሙ የሚችሉት ልባቸውን በእግዚአብሔር ቃል እውነት የሞሉ ብቻ ናቸው። እያንዳንዱ ነፍስ የምርመራ ፈተና ይመጣባታል፥- «ከሰው ይልቅ እግዚአብሔርን ልታዘዝን? ወሳኙ ሰዓት እነሆ ቀርቦአል! እግሮቻችን በማይለወጠውና እንደ አለትም በጠነከረው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ቆመዋልን? ለእግዚአብሔር ትእዛዛትና ለየሱስ እምነት በጽኑእ ተሟጋችነት ለመቆም ተዘጋጅተናልን?

መድኃኒታችን ከመሰቀሉ በፊት እርሱ እንደሚሞትና ከመቃብርም እንደሚነሳ አስቀድሞ ለደቀ መዛሙርቱ ነግሮአቸው ነበር። መላእክትም የእርሱን ቃል በእነርሱ ልብና አእምሮ ለመቅረጽ በአካባቢያቸው ተገኝተው ነበር። ነገር ግን ደቀ መዛሙርቱ ከሮማውያን ቀንበር ጊዜያዊ ነጻነትን ያገኙ ዘንድ ይጠብቁ ስለነበር ተስፋቸውን ሁሉ የጣሉበት ጌታ የውርደት ሞትን ይሞታል የሚለው ሃሳብ ራሱ እነርሱ ሊቀበሉት የማይችሉት ሃሳብ ሆነባቸው። ሊታወሳቸው ይገባ የነበረው ቃል ከአእምሮአቸው ጠፍቶ ስለነበር የፈተና ጊዜ በመጣበት ወቅት ሳይዘጋጁ ቀሩ። የክርስቶስ ሞት ቀደም ብሎ ተነግሮአቸው እንዳልነበረ ተስፋቸው ሙሉ በሙሉ ጠፋባቸው። ስለዚህ ያኔ በክርስቶስ ቃል አማካኝነት ለደቀ መዛሙርቱ ቀድሞ ተገልጾላቸው እንደነበር ዛሬም ለእኛ በትንቢት የወደፊት ነገር ሁሉ ተገልጾልናል። ከምህረት ደጅ መዘጋትና ለመከራ ጊዜ ከመዘጋጀት ሥራ ጋር የተያያዘው የአለም ሁኔታ በግልጽ ይታየናል። ሰይጣን ሰዎች ስለ ደህንነት እውቀቱ እንዳይኖራቸው የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል፤ያም የመከራ ጊዜ ሳይዘጋጁ ያገኛቸዋል።

እግዚአብሔር ወደ ሰዎች ጠቃሚ ማስጠንቀቂያ በሚልክበት ጊዜ ማንኛውም የማመዛዘን ችሎታ ያለው ሰው መልእክቱን እንዲያስተውል ይፈልጋል። ለአውሬውም ሆነ ለምስሉ በሚሰግዱት ሰዎች ላይ የሚደርሰው ፍርድ (ራእይ 14፥9-11) ሰዎች ሁሉ የአውሬው ምልክት ምን እንደሆነ እርሱንም ላለመቀበል ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለማወቅ (ለመረዳት) ትንቢቱን ተግተው ያጠኑ ዘንድ ሊያነሳሳቸው ይገባል። ብዙ ሰዎች ግን እውነትን ላለመስማት ጆሮአቸውን እየደገኑ ወደ ተረት ያተኩራሉ። ሐዋሪያው ጳውሎስ ወደ መጨረሻዎቹ ቀኖች እየተመለከተ እንዲህ ሲል ገልጾአል፥- «ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሱበት ዘመን ይመጣል...» (2ኛ ጢሞ 4፥3)። ይህ ጊዜ ዛሬ መጥቶአል። ብዙ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ እውነትን አይፈልጉም፣ምክንያቱም የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ኃጢያተኛና አለም ወዳጅ የሆነው የልባቸውን ምኞት ይነካባቸዋልና። ሰይጣንም ለነዚህ ሰዎች የሚመኙትን በማቅረብ ያታልላቸዋል።



እግዚአብሔር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ የትምህርትና የተሀድሶ ሁሉ መሠረት አድርገው የሚይዙ ሰዎች በዚህ ምድር ይኖሩታል። የምሁራን አስተያየት፣የሳይንስ ውጤቶች፣የካህናት አብያተ መማክርት እምነትም ሆነ ውሳኔዎች፣ የብዙሃኑ ድምጽ ሁሉ ቢሰበሰብ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ እንኳን ለሃይማኖት እምነት ማስረጃ ሊሆን አይችልም። ማንኛውንም ትምህርት ወይም ትእዛዝ ከመቀበላችን በፊት «እግዚአብሔር አምላክ እንዲህ ብሎአልን?» ብለን መጠየቅ አለብን።

ሰይጣን ሰዎች በእግዚአብሔር ፈንታ በሰዎች ላይ እንዲያተኩሩ ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል። ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን መርምረው ያለባቸውን ግዴታ በማወቅ ፈንታ ጳጳሳትን፣ቄሳውስትንና የሥነ መለኮት ሊቃውንትን እንደመሪዎቻቸው አድርገው እንዲመለከቷቸው ይመራል። ከዚያም የነዚህን መሪዎች አእምሮ በመቆጣጠር ብዙሃኑ በሱ ፈቃድ እንዲመሩ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል።

ክርስቶስ የሕይወትን ቃል ለመናገር በመጣ ጊዜ ተራው ሕዝብ በደስታ ያዳምጠው ነበር። ካህናትና መሪዎች እንኳን ሳይቀሩ በእርሱ አመኑ። ነገር ግን የካህናት አለቆችና የሕዝቡ መሪዎች የእርሱን ትምህርት ለማውገዝና ላለመቀበል ወሰኑ። ምንም እንኳን ላያገኙለት ወንጀል ከርሱ ለማግኘት ቢጥሩም፣ምንም እንኳን የሚናገረው ቃል በጥበብና በመለኮታዊ ኃይል የተሞላ መሆኑን ቢያውቁም ቅሉ፤በርሱ ላይ የነበራቸው የጥላቻ መንፈስ እየባሰባቸው ሄደ። የመሢህነቱንም ግልጽ ማስረጃ ላለመቀበል ወሰኑ። ቢቀበሉማ ኖሮ ደቀ መዛሙርቱ ይሆኑ ዘንድ እውነት ባስገደዳቸው ነበር። እነዚህን የየሱስ ተቃዋሚዎች ሕዝቡ ገና ከሕጻንነት ዘመኑ ጀምሮ እንዲያከብራቸውና እንዲገዛላቸው ተምሮ ነበር። ሕዝቡም እንዲህ ሲሉ ጠይቀዋል፥- «ገዢዎቻችንና ምሁራን ጸሐፊዎቻችን በየሱስ የማያምኑት እንዴት ነው? እርሱ ክርስቶስ ቢሆን ኖሮ እነዚህ አዋቂዎች በተቀበሉት ነበር!»። የነዚህ የሕዝብ መምህራን ተጽእኖ ነበር የአይሁድ ሕዝብ ክርስቶስን እንዳይቀበሉ ያደረገው።

እነዚያን ካህናትና መሪዎች ያነሳሳ መንፈስ ዛሬም በብዙዎች «ሃይማነተኞች ነን» ባዮች እየተገለጸ ነው። እነርሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ልዩ ወቅታዊ እውነቶች ለመመርመር አይፈልጉም። የአባላቶቻቸውን የቁጥር ብዛት፣ያላቸውን ሃብትና ዝና ብቻ በማስመልከት ትክክለኛውን እውነት የሚሰብኩትን እነርሱ «በቁጥር ያነሱ፣ድሆች እና ዝና የሌላቸው እንዲሁም ከአለም ጋር የሚለያይ ትምህርት ያላቸው ናቸው» በማለት እጅግ ዝቅ አድርገው በማየት ይንቋቸዋል።

ክርስቶስ የነዚህ የፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን ስልጣን ተጽእኖ በአይሁዶች መበታተን ብቻ እንደማያበቃ ቀደም አድርጎ ተመልክቶአል። በዘመናት ሁሉ ለቤተክርስትያን እርግማን የሆነውን፤ ሕሊናን ለመግዛት ሲባል የሰውን ስልጣን ከፍ የማድረግን ሥራ አስቀድሞ በትንቢት አይቶአል። ክርስቶስ ፈሪሳዊያንንና የሕግ መምህራንን በጥብቅ ያወገዘውና ሕዝቡ እነዚህን እውራን አለቆች እንዳይከተል የሰጠው ማስጠንቀቂያ ለመጪው ትውልድ እንደ ተግሳጽ (ምክር) ይሆን ዘንድ ተጽፎ ይገኛል። የሮማ ቤ/ክ «መጽሐፍ ቅዱስን የመተርጎም (የማስረዳትና የማስተማር) መብት ለካህናት ብቻ ተሰጥቶአል፤በመሆኑም የእግዚአብሔርን ቃል ለማስረዳት ብቃት ያላቸው ካህናት ብቻ ናቸው» በማለት ተራው ሕዝብ መጽሐፍ ቅዱስ በእጁ እንዳይገባ አድርጋለች። ምንም እንኳን የተሃድሶ እንቅስቃሴ (ሪፎርሜሽን) በወቅቱ መጽሐፍ ቅዱስ ለሁሉም ሰው እንዲዳረስ ቢያደርግም፣የሮማ ቤ/ክ ይዛ የነበረችው ተመሳሳይ መሠረተ አቋም በፕሮቴስታንት ቤ/ክ ያሉትን ብዙ አማኞች መጽሐፍ ቅዱስን ራሳቸው በግል እንዳይመረምሩ አግዶአቸዋል (አሰናክሎአቸዋል)። ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ቤ/ክ እንደተረጎመችው መቀበል እንዳለባቸው ይማራሉ። ምንም እንኳን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ የተጻፈ ትምህርት ቢሆንም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ከመምህራኑ እምነትም ሆነ ከቤተክርስትያናቸው መሠረታዊ ትምህርት ጋር የሚቃረን ሆኖ ካገኙት በጭራሽ አይቀበሉትም።

የሐሰት መምህራንን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ማስጠንቀቂያዎችን የያዘ ቢሆንም የነፍሳቸውን ደህንነት ለካህናት ለማስረከብ የተዘጋጁ ብዙዎች ናቸው። በዛሬው ዘመን ስለሚያምኑት እምነት ምክንያት እንዲሰጡ ቢጠየቁ ከሃይማኖት መሪዎቻቸው ቀድሞ ከተቀበሉት በቀር ሌላ ምክንያት የማያቀርቡ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች አሉ። የመድኃኒትአለምን ትምህርት እጅግም ሳያስተውሉት ያልፉታል። ካህናት በተናገሩት ቃላት ግን ሙሉ በሙሉ ይታመናሉ። ለመሆኑ ካህናት የማይሳሳቱ፣እንከን የሌላቸው ናቸውን? ነፍሶቻችንን እንዲመሩ እንዴት አምነን ለነሱ አደራ እንሰጣለን? ከብልሹው አለማዊ

*በገጽ 8 ይቀጥላል*

# የየሱስ አሻራ ያለበት ለዘላለም አይጠፋም

## ምስክርነት



የተወለድኩበት አገር በጎሙጎፋ ክ/ሀገር በገለብና ሐመር ባኮ አውራጃ በባኮ-ጋዘር ወረዳ በ ውብሀመር በተባለ ቀበሌ ነው። ከትውልድ እስከ እድገቴ የኦርቶዶክስ ቤተሰብ ውስጥ ነው ያሳለፍኩት። ማመንና መዳን ምን እንደሆነ በውል ባላውቅም በተፈጥሮዬ እግዚአብሔርን እጅግ አድርጌ እፈራለሁ።

ገና የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን አጠናቅቄ መለስተኛ ደረጃ ት/ቤ ስማር ሳለሁ ማን እንደሰጠኝና እንዴት እንደሚሠራ፣ለምን ጥቅም እንደሆነ አላውቅም ነበር ቢሆንም «ለትንቢት ድምጽ» በሚሉት አዲስ አበባ በሚገኘው አድራሻ በመጻፍ የመላላክ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ትምህርትን ጀመርኩኝ። ትዝ ይለኛል የትምህርቱ አራሚ ስማቸውን ሲያስተዋውቁኝ «አቶ ጸጋው ደሴ» ይባሉ ነበር። አሁን እንጃ ይኑሩ አይኑሩ በውል አላውቅም። ይህ በእንዲህ እያለ በመሃል በአካባቢያችን እንቅስቃሴዎች ተበራከቱ። ወጣቶች በመሆናችን በመበታተን እኔም በዚህ ምክንያት እከታተለው ከነበረው የመላላክ የመጽሀፍ ቅዱስ ትምህርት ተለየሁ። በወቅቱ በአካባቢያችን በሚገኘው ቤ/ክ ብከታተልም ሁኔታውም ሆነ ወቅቱ አመቺ ስላልነበረ ጠፍቼ በጨለማው አለም ስባዝን በተለያዩ ሱሶች ተይዤ በባርነት ስገዛ ቆየሁ።

ጌታ ታላቅ ነውና የራሱን በጎች ስለሚያውቅ ሲጠራኝ ድምጹን ሰምቼ ፍቅሩ ሲስበኝ የበደልኩት በደል ጸጸተኝና «እንዴት ይቅርታ ማግኘት እችላለሁ? እንዴት ከአምላኬ ጋር መታረቅ እችላለሁ?» ብዬ ሳስብ የነበረኝን ሱስ (ጫት መቃም፣ሲጋራ ማጨስ) ባልተውም በተቀመጥኩበት ቦታ ሁሉ ዘወትር መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ተያያዝኩኝ። በእውነቱ ከሆነ ያነበበ ሁሉ ያውቃል ማለት አይደለም፤ይህ ሥራ የራሱ የጌታ ነውና በቃሉ ተመሰጥኩኝ። ከዚያም ቆራጥ አቋም በመውሰድ የትም ይሁን የትም ቃሉ ወደሚነገርበት ስፍራ ለመሄድ ወሰንኩኝ። በዚያን ጊዜ «የመዳን ቀን ዛሬ ነው ፣ ያመነና የተጠመቀ ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል» የሚለው ትዝ አለኝ። ስለዚህ በወቅቱ የደህንነትን ትምህርት ለስድስት ወራት ያህል በሙሉ ወንጌል ቤ/ክ ተምሬ ተጠመቅሁ። ከጥቂት ቀናት በኋላ በመጀመሪያ ስከታተል የነበርኩት የትንቢት ድምጽ የመጻጻፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ትዝ አለኝ። በተማርኩት መሠረት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ባለመፈጸሜ እግዚአብሔርን የማሳዝነው መሰለኝ። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ስለመፈጸም አስፈላጊነት የደህንነትን ትምህርት የተማርኩበት ቤ/ክ የነበሩትንና ያስተማረኝን ወንድም ደጋግሜ ጠይቄ ነበር። ለዚህ ጥያቄ በቂ መልስ ባለማግኘቴ ከተጠመቅሁ ከአንድ ሳምንት በኋላ ወደዚያ ቤ/ክ መሄድ አቆምኩ። ለምን ከ ቤ/ክ እንደቀረሁ ተጠየቅሁ። የእግዚአብሔር ቃል እንደሚለው ከአስርቱ ትእዛዛት አራተኛውን «ሰንበትን አክብር» የሚለውን ስለማይጠብቁ እንደሆነ ገለጽኩላቸው። ያነጋገሩኝ ወንድሞች ለዚህ መልስ ሲሰጡኝ፥ «ሰንበት በአይሁዳውያን ጊዜ የነበረ ነው፣ዛሬ በክርስቶስ መስቀል ተቸንክሮአል» አሉኝ። «ይህ ታላቅ ስህተት ነው» ስላልኳቸው ከዚያን ጊዜ ወዲህ ደግመው ወደእኔ አልመጡም።

በወቅቱ በወረዳው አድቬንቲስት አይታወቅም ነበር። ከጥቂት ወራት በኋላ ከወላይታ ሶዶ አድቬንቲስት ቤ/ክ አባል የነበሩ አቶ አበበ እና ተክሌ የተባሉ ሰዎች እግዚአብሔር ራሱ መርቶአቸው አጠያይቀው ወደእኔ መጥተው አጽናኑኝ፣በቂ ቃልን አስተላለፉልኝ። በዚህም ምክንያት እነሆ ለ18 ዓመት ያህል ከምፈራው አምላኬ ተለይቼ የነበርኩት እ.ኢ.አ. በ1987 ዓ.ም. በጌታ ጸንቼ ዛሬ ዘጠኝ ዓመት በማስቆጠር ላይ እገኛለሁ። ዛሬ በዚህ በሳወላ ከተማ እኔና ቤቴ በአንድነት እናመልካለን። ቤተክርስቲያንም ለመጀመሪያ ጊዜ ለአራት ዓመታት በግል ወጪ የግለሰብ ቤት በመከራየት ስናመልክ ቆየን። በኋላ ግን እንደሁኔታው በቤታችን ከቤተሰብ ጋር እያመለክን እንገኛለን።

እንግዲህ ዛሬ እኔ ለዚህች መጽሔት አንባቢያን የማስተላልፈው መልእክት ቢኖር፥ ካሳለፍነው ዘመን የአሁኑም ሆነ የወደፊቱ እጅግ አስከፊና አሳሳቢ፤የትንቢትም መፈጸሚያና ማለቂያ ዘመን ስለሆነ የክርስቶስ አሻራ ያለባችሁና ይህን ለምትሹ ሁሉ «ዘመኑን ዋጁ!» አምላካችን እግዚአብሔርን እንፍራ፣ወደ እርሱ እንመልከት፣የጥፋትና የመቅሰፍት ዘመን ስለሆነ በጸሎት እንትጋ! የተሰጠንን የወንጌል አደራ በማስተላለፍም እንትጋ! እግዚአብሔር ከሁላችንም ጋር ይሁን፣ጌታ ይባርካችሁ።◆

ወንድማችሁ ታዬ አበራ፣ ከሳውላ ከተማ

ውድ አንባቢያን!

ይህች የምስክርነት አምድ እግዚአብሔር ሰዎችን እንዴት አድርጎ ከድቅድቅ የኃጢያት ጨለማ አውጥቶ ወደሚደነቅ ብርሃን እንዳመጣቸውና ትእዛዙን ከሚጠብቁት እንዲሁም የሱስን በማመን ከሚጸኑት ሕዝቡ ጋር እንደቀላቀላቸው የምናሳይበት አምድ ነው። የእርስዎንም ታሪክ ጌታ የሱስ እንዴት እንደቀየረውና የሰማይ ቤት ወራሽ እንዲሆኑ እንዳደረገዎ ለአንባቢያን ለማሳወቅ ፈቃድዎ ከሆነ ምስክርነትዎን በጽሑፍ ቢልኩልን በዚህች መጽሔት አማካኝነት ለብዙዎች በረከት ልናውለው እንችላለን።

# ወቅታዊ ዜናዎች በአጭሩ

## <u>የጥንት ጽሑፍ ተገኘ</u>

ከ60-64 ዓ.ም. አካባቢ ባለው ጊዜ እንደተጻፈ የሚገመት የጥንት ጽሑፍ ተገኘ። ይህ በአራሜይክ ቋንቋ የተጻፈው «ያዕቆብ፣የዮሴፍ ልጅ፣<u>የየሱስ</u> ወንድም» የሚለው ጽሑፍ፤የየሱስ ስም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ከተጠቀሱባቸው ምንጮች የመጀመሪያውን ቦታ የያዘ ነው ተብሎ ይገመታል። (ANN)

## <u>SMS - Bible</u>

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በሞባይል ቴሌፎን በአጭር መልእክት (SMS) መላላክ ይቻል ዘንድ በኖርዌይ የሚገኘው ጎስፐል ሰርች የተባለው የኢንተርኔት ፕሮቫይደር እጥር ምጥን ያለ መጽሐፍ ቅዱስ ለማውጣት በዝግጅት ላይ ይገኛል። (FR)

## <u>100 ዓመታት በቻይና</u>

በሆንግኮንግ ያለችው የ7ኛ ቀን አክባሪ አድቬንቲስት ቤ/ክ የተመሠረተችበትን 100ኛ ዓመት አከበረች። የመጀመሪያው ጀነራል ኮንፈረንስ (የመላ አድቬንቲስት ዓለም አቀፍ ቢሮ) በ1902 ዓ.ም. ወደ ቻይና የተላከው ወንጌላዊ «ፓስተር ጃኮብ ኔልሰን አንደርሰን» ይባል ነበር። ፓስተር ጃኮብ ከአንድ ዓመት ቆይታው በኋላ የመጀመሪያዎቹን በጌታ ያመኑትን ሰዎች አጠመቀ። በዚያኑ ዓመት የመጀመሪያዋን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያንን መሠረተ። ዛሬ በኮሙኒስት ቻይና አገር 300 000 7ኛ ቀን አክባሪ አድቬንቲስቶች ይገኛሉ። በሆንግ ኮንግ ከተማ ብቻ በ16 ቤ/ክኖች 3800 አባላት ይሰበሰባሉ። በተለያዩ ከተማዎች ውስጥ ደግሞ ቤተክርስቲያንዋ ዩኒቨርሲቲዎችን፣1ኛና 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶችን፣የሕጻናት መዋያዎችን፣ማተሚያ ቤቶችን፣የራዲዮና የቴሌቪዥን ጣቢያን እንዲሁም ሆስፒታሎችን ታስዳድራለች። (APD)◆

# የትንቢት ቃል


Yetnbit Kal
P.O.Box 1749
90006 Nuernberg
Germany

Editors:
Dawit Mehari
Dawit Mengistu

Tel & Fax 0049 - 911- 41 57 89
Tel & Fax 0049 - 89 - 22 24 48
E-Mail: dawit.mehari@mail.com
E-Mail: dawitmengistu@web.de


ይህች «የትንቢት ቃል» የምትለው የአድቬንቲስት መጽሔት በጀርመን አገር ተዘጋጅታ በየሶስት ወር ትወጣለች። አላማዋም በአገራችንና በተለያዩ አህጉራት የሚገኙትን ወገኖቻችንን ለየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ለማዘጋጀት ነው። ምንም ዋጋ የማይከፈልባት በነጻ የምትላክ እንደሆነች ልንገልጽልዎ እንወዳለን። ስለዚህ ለእርስዎም ሆነ ለሌሎች ጽሑፉ እንዲደርሳቸው ለሚፈልጉት ሰዎች አድራሻዎችን ቢያሳውቁን መጽሔቱን እንልካለን።

በዚህች መጽሔት መልእክት ተባርከው እንደሆነና አስተያየትም ሆነ ጥያቄ ካለዎ ሃሳብዎን ቢገልጹልን በጣም ደስ ይለናል።

ይህንን የጽሑፍ አገልግሎት በገንዘብ ለመደገፍ የምታስቡ ሁሉ በዚህ የባንክ ቁጥር መጠቀም ትችላላችሁ። ለድጋፋችሁ በቅድሚያ ከልብ እናመሰግናለን እግዚአብሔር ይባርካችሁ!
Sparkasse Nürnberg,
Yetnbit Kal,
Account Nr.: 2 059 932
BLZ: 760 501 01

## *መጠበቂያው የእግዚአብሔር ቃል*

*(ከገጽ 6 የዞረ)*

መንገድ ለመውጣት የሚያስችለው የሞራል ድፍረት እጦት ብዙዎች አካሄዳቸውን ከምሁራን ጋር እንዲያደርጉ ይመራቸዋል። እውነትን ራሳቸው በግል መመርመርን ስላልፈለጉ ተስፋ በሚያስቆርጥ መንገድ በሐሰት ሰንሰለት ይታሰራሉ። እነርሱ የወቅቱ እውነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ እንደተጻፈ ያያሉ፣የመንፈስ ቅዱስ ኃይልም በመልእክቱ ውስጥ እንዳለ ይመለከታሉ፤ቢሆንም የካህናቱ ተቃውሞ ከተገለጠላቸው ብርሃን እንዲያሸሻቸው ይፈቅዱለታል። ምንም እንኳን አእምሮአቸውና ሕሊናቸው ቢቀበልም እነዚህ የተታለሉ ነፍሳት ካህናት አገልጋዮቻቸው ከሚያምኑት እምነት የተለየ ለማመን አይደፍሩም። በመሆኑም የግል ውሳኔያቸውና ዘላለማዊ ፍላጎታቸው በሌላ ሰው ቁጥጥር ስር ሆኖአል።

ሰይጣን የእርሱ ምርኮኞች የሆኑትን አጥብቆ ለመያዝ በሰብአዊ ተጽእኖ አማካኝነት የሚሠራባቸው ዘዴዎች በርካታ ናቸው። የክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ከሆኑት ጋር በፍቅር የሐር ክር በማያያዝ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ሰዎች የራሱ ያደርጋቸዋል። ይህ ወዳጅነት በማንኛቸውም መልኩ ቢሆን (የወላጅና ተወላጅ ዝምድና፣የትዳርም ሆነ የማሕበራዊ ወዳጅነት) ወጤቱ ያው ነው። የእውነት ተቃዋሚዎች ሕሊናን ለመግዛት (በቁጥጥር ስር ለማዋል) ኃይላቸውን ይጠቀማሉ። በእነርሱ ተጽእኖ ስር የወደቁትም ነፍሳት ያመኑበትን ተቀብለው ግዴታቸውን በሥራ ላይ ለማዋል በቂ ድፍረት ወይም ነጻነት የላቸውም ...።

ይቀጥላል።

## የጥያቄዎ መልስ

### «ዛሬም ክርስቲያኖች ሰንበትን ማክበር አለባቸውን?»

*አቶ ፐ.ነ. ከጀርመን*

ፖርቱጋሎች አፍሪካን በወረሩበት ጊዜ ኢትዮጵያውያኖች ክርስቲያኖች በመሆናቸው ተደነቁ። በዛ ላይ ደግሞ ኢትዮጵያውያን እሁድን ሳይሆን ሰንበትን (ቅዳሜን) ሲያከብሩ ሲመለከቱ ግራ ገባቸው። እ.ኤ.አ. በ1534 ዓ.ም. የኢትዮጵያ መልእክተኞች በሊሳቦን (የፖርቱጋል ዋና ከተማ) በነበረው ቤተ መንግሥት ስለዚህ ጉዳይ ጥያቄ ሲጠየቁ የመለሱት መልስ ይህ ነበር፦ «እግዚአብሔር አለምን ፈጥሮ በ 7ኛው ቀን ስላረፈ እና ይህንን ቀን ቅዱስ ስላለው፣ይህንን ቀን አለማክበር ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ የሚጸናውን የእግዚአብሔርን ፈቃድና ትእዛዝ ይቃረናል። ምክንያቱም ክርስቶስ የመጣው ሕግን ለመሻር ሳይሆን ለመፈጸም ነው። ስለዚህ ሰንበትን መጠበቃችን አይሁዶችን ለመከተል (ለመኮረጅ) ሳይሆን ክርስቶስንና የሐዋሪያትን ትምህርት ለመታዘዝ ነው።» (ዋቢ፦ ዶ/ር ጀደስ, ቸርች ሂስትሪ ኦፍ ኢትዮጵያ, ገጽ 87-88)

ሰንበት ለኢትዮጵያውያን እግዚአብሔር የለየው፣የባረከውና የቀደሰው የፍጥረት መታሰቢያ ቀን ነበር (ዘፍ 2፥2-3 ይመልከቱ)። «ባረከው እና ቀደሰው» የሚሉት ቃላት በዚያን ጊዜ ለነበሩት ሰዎች ብቻ አልነበረም። እግዚአብሔር ሰንበትን ለሰው ዘር ሁሉ ነው የሰጠው፤ዛሬም ቢሆን ሰንበትን አላስቀረም። የሰንበት ትእዛዝ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ለሕዝቡ ከሰጠው 10ቱ ትእዛዛት አንዱ ነው (ዘጸ 20፥1-18)። ከትእዛዛቶቹ ረጅሙ እና በመካከል ላይ ያለ እርሱ ነው። እንዲያውም ይህንን ትእዛዝ እግዚአብሔር ራሱ በእጁ በድንጋይ ጽላት ላይ ከጻፈ በኋላ «ይህ የፈጣሪነቴና የምቀድሳችሁ እኔ እንደሆንኩ የሚያሳይ የዘላለም ምልክት ነው» አለ (ዘጸ 31፥12-18)። እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ቃላት በአገልጋዮቹ አማካኝነት እንዲጻፍ አደረገ። 10ቱን ትእዛዛት ግን ራሱ በእጁ ጻፈ። ይህም እነዚህ ትእዛዛት (ሰንበትንም ጨምሮ) ለእሱ በጣም አስፈላጊ መመሪያዎች እንደሆኑ ያሳያል።

> **«የምቀድሳችሁ እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩ ታውቁ ዘንድ በእኔና በእናንተ ዘንድ ለልጅ ልጃችሁ ምልክት ነውና ሰንበቶቼን ፈጽሙ»**
> (ዘጸ 31፥13)

የሱስ እነዚህን ትእዛዛት በተራራው ስብከት ላይ አላስወገዳቸውም (አልሰረዛቸውም) እንዲያውም እስከ አለም መጨረሻ እንደሚጸኑ አረጋገጠ (ማቴ 5፥17-20)። እንዲያውም ሁለት ምሳሌዎችን በመስጠት የበለጠ አጠነከራቸው (ማቴ 5፥21,22,27,28)። የሱስ ዘወትር ሰንበት ወደ ጸሎት ቤት የመሄድ ልምድ ነበረው (ሉቃ 4፥16)። በዛ ላይ ደግሞ ከሞቱ እና ከትንሳኤውም በኋላ ሰንበት መጠበቅ እንደሚገባው ተናገረ በመሆኑም ደቀ መዛሙርቱም በስደት ጊዜ ሽሽታቸው በሰንበት ቀን እንዳይሆን እንዲጸልዩ መከራቸው (ማቴ 24፥20)። ነብዩ ኢሳያስ እንደጻፈው ከሆነ አማኞች ሰንበትን በአዲሲቷ ምድር እንኳን ሳይቀር ይጠብቃሉ (ኢሳ 66፥22-23)። ስለዚህ ሐዋሪያት በየሰንበቱ መሰበካቸውና ማስተማራቸው አያስገርምም (ሐዋ 18፥1-4)። ሰንበት በታሪክ ውስጥ የተሰረዘ ቢሆን ኖሮ ይህንን በተመለከተ በሐዋሪያት ቤ/ክ መገረዝንና ሌሎች የአይሁድ በዓላትን በተመለከተ ከተነሳው ክርክር የበለጠ ከባድ ክርክር በተነሳ ነበር። በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሰንበት መሰረዝ ምክንያት ስለተነሳ ክርክር ተጽፎ አናገኝም። የሰንበት ክርክር የተነሳውና ሰንበት መከበር የተተወው ከብዙ ዓመታት በኋላ (321 ዓ.ም.) ክርስቲያኖች ከአይሁድ ሃይማኖት ራሳቸውን ለማራቅ (ለመለየት) በጀመሩበት ጊዜ ነበር። ◆

**ከእስልምና ወደ ክርስትና**
ሸህ ዘካሪያ ጂብሪል
(አለቃ ነዋየክርስቶስ)

በፓ/ር
ጥሩነህ ወ/ሥላሴ